ማቴወስ 27÷9

በነቢዩ በኤርሚያስ የተባለው ?

CHRISTIAN ANSWER CHANNEL
HENOCK A.B



ማቴወስ 27 ÷ 9

በነቢዩ በኤርሚያስ የተባለው ?

በተለያዩ ማህበራዊ ገጾች በተደጋጋሚ ሲጠየቁ ከነበሩ ጥያቄወች መካከል አንዱ ማቴ 27÷9 ነው ።። ብዙወች 66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ግዶሎ ነው ብለው ሊሞግቱ ሲነሱ እነኚህን አይነት ጥያቄ በማንሳት ከ66 ቱ አሳዩን በማለት ይጀምራሉ ።። ከ66ቱ ከሌለ 66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ጎዶሎ ነው ለማለት ይጣደፋሉ በርግጥ 81 ሆኖም የማይመልሱት አለ ስለዚህ በእነሱ እሳቤ መጽሐፍ ቅዱስ 66ትም ሆነ 81 ጎዶሎ ነው ማለት ነው ።። ይሄ የመጽሐፍ ቅዱስን አላማ ካለመረዳት የሚመነጭ ነው ።። መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፈ እግዚአብሔር ለልጆቹ የሚያስፈልገው እውነት የገለጠበት መጽሐፍ ነው ።።

ከጠያ-ቂ-ወቻችን ከተነሱ ጥያቄወች መካከል በ@christian Answer የቴሌግራም ቻናልና በfacebook page ምላሾቻችንን እያቀረብን ነው ዛሬም ማቴወስ 27:9 ኝን እነሆ ይዘን ቀርበናል ።።

- ማቴወስ 27÷9

የማቴወስን ወንጌል የጻፈው ከአስራ ሁለቱ ሐዋርያት መካከል የነበረው ማቴወስ ነው ።። ማቴዎስ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች መፈፀማቸውን ከሌሎቹ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ይልቅ 12 የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ፍጻሜ ማግኘታቸውን ዘግቧል :: ከእነኚህ ፍጻሜ ካገኙ የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች መካከል አንዱ ማቴዎስ 27:9 ነው ።።

" በዚያን ጊዜ በነቢዩ በኤርምያስ የተባለው። ከእስራኤል ልጆችም አንዳንዶቹ የገመቱትን፥ የተገመተውን ዋጋ ሠላሳ ብር ያዙ፥"

(የማቴዎስ ወንጌል 27:9)

ይሄንን ጥቅስ ትንቢተ ኤርሚያስ ውስጥ በቀጥታ አናገኘውም ነገር ግን በእርጋታ ማጥናት ከቻልን ምላሹ በዚሁ በ66ቱ መጽሐፍት ውስጥ አለ

ማቴዎስ 27÷9 ኝ ማቴወስ የጠቀሰው የዘካርያስ 11÷12-13 እና የኤር 32:6-8, 19÷1-13 ጥምር ይሆናል ። ነገር ግን ማቴዎስ ከአቢይ ነቢያት(major prophet) መካአል አንዱ የሆነው ኤርምያስ ነው ብሏል ።

- አቢይ ነቢያት(major prophet)

የሚባሉት ኢሳያስ ፣ኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ዳንኤል ናቸው የተባሉበትም ምክንያት በብሉይ ኪዳን ባሏቸው የመጽሐፍ ትልቅነትና በይዘቱ ሰፊ በመሆኑ ከሌሎቹ ሰፋ ያለ በመሆኑ ነው ።

ስለዚህ ማቴዎስ የዘካርያስንና የኤርምያስን ትንቢት በማጣመር ኤርሚያስ ተናገረው ብሎናል ይህ የመጀመሪያ አደለም ማርቆስም በሌላ ክፍል ሁለት ትንቢቶችን በማጣመር አብይ ነቢይ በሆነው ነቢይ ስም ይነግረናል እስቲ እንመልከተው

- ማርቆስ 1:3

" እነሆ፥ መንገድህን የሚጠርግ መልክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ ተብሎ በነቢዩ በኢሳይያስ እንደ ተጻፈ፥"የማርቆስ ወንጌል 1:2-3

ማርቆስ ትንቢቱ የተገኘው ከነቢዩ ኢሳያስ ነው ይበል እንጂ ጥቅሱ ከሁለት ጥቅሶች በጥምረት የተገኘ ነው ።

- ✓ የመጀመሪያዎቹ ሁለት ስንኞች የተወሰዱት ከሚልክያስ 3÷1 ነው ።

" እነሆ፥ መልእክተኛዬን እልካለሁ፥ መንገድንም በፊቴ ያስተካክላል፤ እናንተም የምትፈልጉት ጌታ በድንገት ወደ መቅደሱ ይመጣል፤ የምትወዱትም የቃል ኪዳን መልእክተኛ፥ እነሆ፥ ይመጣል፥ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር። " ትንቢተ ሚልክያስ 3:1

✓ ሶስተኛው ስንኝ ግን ከኢሳያስ 40÷3 የተወሰደ ነው ::

" የአዋጅ ነጋሪ ቃል። የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ ጥረጉ፥ ለአምላካችንም ጐዳና በበረሀ አስተካክሉ።"(ትንቢተ ኢሳይያስ 40:3)


ማርቆስ እነኚህን ሁለት ጥቅሶች በማጣመር አብይ ነብይ(major prophet) የሆነው የነቢዩ ኢሳያስ ነው ብሎ በማርቆስ 1÷3 ላይ ዘግቦልናል ::

" እነሆ፥ መንገድህን የሚጠርግ መልክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ ተብሎ በነቢዩ በኢሳይያስ እንደ ተጻፈ፥"
(የማርቆስ ወንጌል 1:2-3)


✓ የኦርቶዶክስ መጽሐፍት ስለዚ ምን ይላሉ ?

ብዙ ሊቃወንትን በማፍራት የምትታወቀው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በሊቃውንቶቿ ተጠንቶ በተለያዩ ጊዜያት በታተመ መጽሐፍ ቅዱስ ለማቴወስ 27÷9 በግርጌ ማስታወሻ በማጣቀሻነት ያስቀመጡት የብሉይ ኪዳን ክፍል ዘካርያስ 11÷12-13 እና ኤር 19-1-12,32- ነው ::

- አዲስ ኪዳን በ1879 የታተመ




አዲስ ኪዳን ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ቅጂ




፷፤ ተመከረም፡ የጭቃ፡ ሰፊ፡ምድርም፡ ᵃግዙፍት፡
ለንግደት፡መቃብር። ᵃየሐዋ፡፭፤፲፱።
፷፤ በለዚህም፡ ያ፡ምድር፡የደም፡ ምድር፡ተብሎ፡
ተጸራ፡ እስከ፡ ዛረ።
፱፤ በዚያን፡ ጊዜ፡ ተፈጸመ፡ በነቢዩ፡ በኤርምያሰ፡
የተባለው፡ እንደ፡ሀ፡ ሲል። ሠላሳውንም፡ ቅርቭ፡ወሰ
ደ፡ የክቡረን፡ ዋጋ፡ የእሥራኤል፡ልጆች፡የተሰማሙ
በትን። → ዘካ፡ ፲፩፤ ፲፪፤ ፲፫፤፤ ኤር፡ ፴፫፡ ፮፤፱
፲፤ ሰለ፡ ጭቃ፡ ሰፊ፡ ምድርም፡ ሰጡት፡ እግዚአብ
ሔር፡እንደዘዘኝ።
፲፩፤ የሱሰም፡ በኩሙ፡ ፈት፡ቀመ። ኩሙም፡ ጠየ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ 81ዱ መጽሐፍ ቅዱስ በ2000 ዓም የታተመ



እንዲሁም በተጨማሪ ለማርቆስ 1÷3 በግርጌ ማስታወሻ ያስቀመጡት የብሉይ ኪዳን ክፍል

ለ ማርቆስ 1:2 ~ ሚልክያስ 3÷1
ለ ማርቆስ 1:3 ~ ኢሳያስ 40÷3



ይህ ማለት የኦርቶዶክስ ሊቃውንቶች ለማርቆስ 1:3 ትንቢት ሚልክያስ 1÷3 እና ኢሳያስ 40÷3 በጥምረት በማድረግ ማርቆስ በማርቆስ ወንጌል 1÷2-3 ላይ እንደጠቀሰ ያምናሉ ። በተመሳሳይ ለማቴዎስ 27÷9 ያስቀመጡት የግርጌ ማስታወሻ ዘካርያስ 11 እና ኤር እንደሆነ ያምናሉ ።

ስለዚህ የቀደሙትም ሆኑ አሁን የ2000 ዓምየ81ዱ እትም ያዘጋጁ የኦርቶዶክስ ሊቃውንት ይይሄንን በማመናቸው በመጽሐፍ ቅዱስ በግርጌ ማስታወሻ በግልጽ አስቀምጠዋል ። ይሄ ደግሞ ለማቴዎስ 27÷9 ምላሽ ከ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ አገኘን ማለት ነው የኦርቶዶክስ ሊቃውንትም ምላሹን ከ66ቱ ብቻ አስቀምጠዋል ።

በ2000 ዓም የታተመው የኦርቶዶክስ 81ዱ መጽሐፍ በቤተክርስቲያኗ ሊቃውንት ሲዘጋጅ በማውጫው ላይ ከተዘረዘሩት 81 የመጽሐፍት ዝርዝረር ውስጥ ተረፈ ኤርምያስ፣ ተረፈ ባሮክ ተካቶ እያለ ስለ ምን እንደ አንዳንድ የማቴዎስ 27÷9 ትንቢት በተረፈ ኤርምያስ (ተረፈ ባሮክ) ያለው ነው ብለው እንደሚሟገቱ ሰወች ለማቴዎስ 27÷9 በግርጌ ማስታወሻ ዘካርያስ 11÷12-13 ን በማስቀመጥ ፈንታ ስለ ምን ተረፈ ኤርምያስን(ተረፈ ባሮክ) አላስቀመጡም ?

በ2000 ዓም በታተመውም ሆነ ከዛ በፊት ባለው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ውስጥ ሊቃውንቶቹ ለማቴዎስ 27÷9 ያስቀመጡት የግርጌ ማስታወሻ ዘካርያስ 11÷12-13ን ነው እኛም የምንቀበለውና የምናምነው ይህንን ነው ። ስለዚህ ልክ እንደ ኦርቶዶክር ሊቃውንቶች እኛም ለማቴወስ 27:9 ምላሻችንን ከ66ቱ መጽሐፍት አቅርበናል ። ማንም ኦርቶዶክስ ማቴዎስ 27:9 በዘካርያስ 11:12-13 ላይ አደለም ብሎ ሊምግቱን ሲመጣ በቅድሚያ የራሱን ሊቃወንት አባቶች መሞገት ይኖርበታል ።

ይቀጥላል .....

CHRISTIAN ANSWER CHANNEL

ከተለያዩ ማህበራዊ ገጾች ለሰበሰብናቸው ጥያቄወች ምላሽን የምንሰጥበት የቴሌግራም ቻናሎቻችን

- @Christian_Answer
- @chrustianAnswer
- @answer4u

በFacebook **ገጻችንም ያጀኑናል**

- christian Answer

ለአስተያየት ፣ ለምክር ፣ ለተግሳጽ

@Henock4 **ያግኙን**

02/01/2013 **አም** AA